የሰ/መ/ቁ. 50182

ግንቦት 13 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአዲስ አበባ ቁራዎች ድርጅት - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ አበበ ተፈራ ይልማ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ኀዳር 2 ቀን 2002 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በሥጋ አከፋፋይ ቡድን መሪነት ሲያገለግል መቆየቱን ገልፆ አመልካች ከግንቦት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ለሥራው ብቁ አይደለህም በማለት ወደ **በፌብልት** ሰራተኛ 11 አዛውረውኛል፡፡ ስለዚህ ወደ ነበርኩበት የሥራ መደብ እንዲመልሰኝ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የድርጅቱ ደንበኞች ቁጥር በመቀነሱ ምክንያት በተደረገው ጥናት በእርድና ሥርጭት ክፍል ችግር ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል ስለዚህ ሥራና ሰራተኛን ለማገናኘት ሰራተኞችን በህብረት ስምምነቱ መሰረት በመመደብ እየሰራን የምንገኝ ስለሆነ የጣስነው ሕግ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ የተማመኑ በመሆኑ ስለጥናቱ ለማስረዳት የተዘረዘሩ ምስክሮች መስማትም ሆነ የጥናት ሰነዱን አስቀርቦ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውም በማለት በጥናቱ የከሳሽ (ተጠሪ) ችሎታ ምንም ሳይሆን ጠቅላላ የድርጅቱ ችግር የተገለፀ በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የሥራ መደብ በማዛወር ማሰራቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ አመልካች ተጠሪን ወደ ቀድሞው የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የቡድን መሪነት የሥራ መደብ እንዲሰራ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ሰራተኞችን የበለጠ ውጤታማ በሚሆኑበት የሥራ መደብ ጥቅምና ደረጃቸውን ሣይቀንስ አዛውሮ ማሰራት የአሰሪው መብትና ሥልጣን ነው፡፡ ተጠሪ አሁን የተመደበበትና የተዛወረበት የሥራ መደብ ደረጃ ስድስት የሆነና ተመሣሣይ ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤት አሰሪው ሰራተኞቹን አዛውሮ የማሰራት ህጋዊ ሥልጣንና በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን በመተላለፍ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝን በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በነበርኩበት የሥራ መደብ የሥራ ችሎታ ማነስ ያለበኝ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የአዋጅ ቁጥር 377/96 እና የሕብረት ስምምነቱን ድንጋጌዎች በማገናዘብ የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በአመልካች ድርጅት አግልግሎት የሚፈልጉ ደንበኞች መቀነስ ዋናው ምክንያት የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የሚሰጠው ክፍል ችግር ያለበት መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ምንም እንኳን አመልካች

ከሃያ በላይ የሚሆኑ የእርድና የሥጋ ስርጭት አገልግሎት የቡድን መሪዎች ያሉትና ለድክመቱ ተጠሪ በግል ኃላፊ ናቸው ባይባልም አመልካች የጥናትቱን ውጤት መነሻ በማድረግ ችግሩን ለማስወገድ አስፈላጊ ነው የሚለውን አስተዳደራዊ ማስተካከያ በመውሰድ ድርጅቱን ትርፋማነት ማስቀጠል ይገባዋል፡፡

አመልካች ተጠሪን ከነበሩበት የሥራ መደብ ተመሣሣይ ደረጃ ደመወዝና ጥቅም ወደአለው የሥራ መደብ አዛውሮ ለማሰራት የወሰደው አስተዳደራዊ ማስተካከያ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ያከናወነው ተግባር ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች በሕጉ በግልጽ የተፈቀደለትን አስተዳደራዊ ተግባር እንዳይፈጽም ክስ የሚያቅርብበት ምክንያት የሌለ ሲሆን በተመሣሣይ የሥራ መደብ ተዛውሮ በመሥራቱ የተነካበት መብትና ጥቅም የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ሌሎቹ የእርድና የሥጋ ሥርጭት የቡድን መሪዎች ሣይዛወሩ እኔ ተዛወርኩ በሚል ምክንያት በመነሣሣት ያቀረበው ክስ የክስ ምክንያት የሌለው በመሆኑ ከጅምሩ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 33 ንኡስ አንቀጽ እና በፍታብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 231 መሰረት መዝጋት ነበረባቸው፡፡

የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች የድርጅት አስተዳደር ሥልጣን በመጋፋት ተጠሪ ወደ ሌላ ተመሣሣይ ደረጃ ወደ አለው የሥራ መደብ በመዛወራቸው የቀረባቸው የደመወዝ ወይም ሌላ ህጋዊ ጥቅም ያለመሆኑን ባላሥረዳበት ሁኔታ ሌሎቹ የቡድን መሪዎች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አልተዛወሩም፣ ተጠሪ የችሎታ ማነስ ያለበት ስለመሆኑ አላስረዳህም በሚል ምክንያት አመልካች ተጠሪን ወደ ቀድሞው የሥራ መደብ አዛውሮና መድቦ እንዲያሰራ የሰጠው ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ 2 የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የተጠሪ የሥራ ደረጃ ደመወዝና ጥቅም በማይነካ ሁኔታ ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ የማሰራት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸ ይቻሉ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ